# አዳፍኔንም መክሸፍንም ነው ያየሁበት — ዳዊት ዳባ

September 12, 2015 -

## :Tuesday, September 01, 2015

*መማር ካለብኝ እየጠየኩ; እየተከራከርኩ;እየተወቀጥኩም እማራለው እንጂ ዝም ብዬ አልማርም።ዝም ብዬም አልስማም። ዝም ብለህ ተገዛ፤ዝም ብለህ እመን;ዝም ብለህ ተከታይሁን.... ብቻ ዝምብለህን አስከትለው የሚመጡ ነገሮች ሁሉ አልቀበልም፡፡ ከመፀሀፉ ልዋስና ያዳፍኔ ባህሪዎች አድርጌ ነው የምወስዳቸው። ናቸውም። ለማዳፈን መሳርያ እንጂ ቃላትና ከመሳርያ ውጪ ያሉ ተጽኖ ማሳደርያ መንገዶች ጉልበት አይሆኑም ትክክል አይመስለኝም።እንደውምየገዘፈ ጉልበት እላቸው። ይህው አሁን ማን ይድፈር። ፀጥ እረጭ። እኔም መክሸፍን ለመተቸት በሞከሩት ላይ የመልስ ምቱን ስላየው ሳልፈራ ግን አይደለም።ግን የግድ ማድረግ ነበረብኝ።የመጀመርያው ምክንያቴመፀሀፉ ውስጥ ዋና የሆነውን ቁምነገር እኔ በተለየ አቅጣጫየተረዳሁት ወይ አየው የነበረ ስለሆነ ነው። በዋናነት ግንማጥቃት ስላለበት ነው። የተለመደ እየሆነ የመጣውጦር ውርወራ ስላለው ነው።*

*“እንዴት” የሚለውን መንደርደርያ ገና አብዘተን በማንጠይቅበት ሁኔታ ሌሎች በሁሉ ነገሮች ላይ ጠይቀው መልሶች አሏቸው።ዛሬም መልስመፈለጉን በርትተውበታል። እንዳንቀደም  ካደረጉን ምክንያቶች ውስጥ አንዱና ዋንኛው “እንዴት” ሲሉ አብዝተው የሚጠይቁ በመሆናቸው ነው። ጠቃሚ ነው ጎጂ የሚለው እንዳለ ከዶሮ ጋር እንዴት ፍትዎት እንደሚፈፀም ሁሉ መልስ አለ። እንዴት ያሳ መረቅ እንደሚሰራ ፤ የተሰበረ ቦርጭማ እንደሚጠገን፤ የእግር ጠረን መከላከል እንደሚቻል። አገዛዝን መገርሰስ እንደሚቻል። ብቻ ለሁሉም ነገሮች አጥጋቢ ካነሰም መነሻ የሚሆን መልስ ሰርተዋል። ይህ የሚስረዳንአብዝተው ‘እንዴት” ሲሉ መጠየቃቸው ብቻ ሳይሆን፤ መፍትሄ ፍለጋ ላይ፤ ለአዲስ ሆነ ለተሻሻለ ፈጠራ ባጠቃላይ ለሁለንተናዊ የሰው ልጅ እድገት  መነሻም ሚስጥር አድርገው እንደወሰዱትም ነው።*

*ወደኛ ሲመጣ በዋናነት “ማወቅ”፤ “እውቀት” አድርገን የወሰድነው፤ ጊዜ ወስደን ልንመረምረው፤ ልንወያይበት፤ ልናነብበት፤ አልፈንም ቡጢ መሰናዘር ድረስየሚመስጠን ታሪክ ነው።“መቼ?”፤ “ማን?”፤ “እንዴት”፤ “ምን”  ከሚሉ መጠየቂያዎች ከተነሳን ሁሌም በሚሰኝ ደረጃ ስለዛሬ ወይ ስለነገ ሳይሆን  ስለትናንትና ነው። ለዛሬና ነገ መፍትሄ ከትናንት መነሻ ማድረጉ አንዳንዴም ሙሉ በሙሉ ካልተቀዳ ማለታችን  መፍትሄ ፍለጋ ላይ ከባድ ችግር ሆኗል። ይህ በራሱ ከፉም ከባድም ችግር ሆኖ እያለ የባሰ የከፋ የሚያደርገው አብዝተን ከትናንት ጋር ፍቅር ላይ በመውደቃችንና  ዛሬን ወይ ነገን አናውቀውም። በቂ በሚሰኝ አኳሐን ጠይቀንበት ችግሩም መፍትሄውንምልንረዳው ሆነ ሊታየን አልቻለም። ከሞከርንምመፍትሄ ብለን የምንሰራውወደፊት ሊያስኬደንና የማያዳግም መሆን አይደለም አንድ ክረምት ሊያሻግረን አልቻለም። እዚህ ላይ ከትናንት ስላልተነሳን ነው የሆነ ጊዜ ላይ እንግዳ በሆነው ሶሻሊዝም የተጠመቅነው የሚል መከራከርያ ዋና ሆኖ መምጣቱ አይቀርም። እሱም ቢሆን ሲጀምር የኛ አይደለም። ይባስ ብሎም ከትናንትና የተቀዳ ነው። ለዛሬና ለነገ በተገቢው ከታሰበበት አይደለም ከሌላ አገር የተቀዳ ከኛም ከትናንትልንቀዳው ወይ ፍፁም ተመሳሳይ ሆኖ ልንጠቀምበት የሚቻለን መፍትሄ የለም። “ ሶሻሊዝም የተንኮታኮተበት አንዱ ምክንያት አንዴ የሆነ ጊዜላይ የተቀመጠ መፍትሄ ሁሌም ሁሉም ቦታናችግሮች ላይ  ይስራል የሚልይዘት ስላለው ነው።*

እዚህ ጋር ነበርኩ። ስጨምር ስቀንስ እያለው ነው መስኮቴን አንኳክቶ ባልንጀራዬ መፀሀፉን ያዋሰኝ።  ከዛም ማንበብ ነው የቀጠልኩት።ከላይ ያለው ሀሳብ በወረቀት ለማስቀመጥ እንዳሰብኩት ቀላል ባይሆንልኝም የዛሬ አይደለም። ውስጤ ብዙ ቆይቷል። በተለያየ መንገድ ስገለፀው የነበረ ነው።ታዲያ አዳፍኔን ይህን ሀሳቤን ይመታዋል። ይገለባብጠዋል።

*“በዋናነት የመክሸፍ ምንጭ ሁለት ይመስለኛል።አንደኛው ትናንትን አለማስታወስ ሁለተኛው ነገን አለማሰብ።” ገጽ* **61** *ሁለተኛ ምእራፍ ላይ።*

እዚህ ላይ ነገን አለማሰብ የሚለው ምክንያት ቢሆንም ሙሉ በሙሉ ማለት በሚያስችል መፀሀፍ ትኩረት ያደረገውና አጉልቶ የሚያሳየን ትናንትን አለማወቅ የሚለውን ነው።  እኔ ዋና መሆን አለበት ብዬ የታሰበኝ የነበረው ደግሞ ዛሬን አናውቀውም ነው። ነገንም እንዲሁ።መፀሀፉ ደግሞ ዛሬን ብቻ ነው የምናውቀው ነው የሚለው። ለዚህ ነው ገለባብጦብኛል ያልኩት። የተራራቁ በቀላሉ ሊስማሙ የማይችሉ ልዩነቶች ሆኑብኝ።እንዳናምታታ ትናንት መታወቅ የለበትም አይደለም ክርክሬ። አንድ ህዝብ ትናንትናን ማወቅ ያለበት ምን ያህል ነው**?** ስንል እኛ የሚያስፈልገንን ያህል አይደለም  ከበቂ በላይ ትናንትን እናውቀዋለን ነው መልሴ። ትናንት ለመኖር ግድ እንደሚሉት አየርና ምግብ አይነት አድርገንዋል ነው። ትናንት ሙሉ ጉልበታችን፤ እውቀታችን፤ ጊዜያችን የሚጠፋበት ሆኗል ነው። ዛሬን በትንሹ ላዛውምበዜናናበመተረክ ደረጃነው የምናውቀው። ያሉ ችግሮች ላይ መፍትሄን ከመስራት አኳያ ገና አናውቀውም ነው። ነገንም እንዲሁ።  ይህ የሆነበት ምክንያት ሁለንተናዊ በሆነ ሁናቴ በትናንት በመያዛችን ነው የሚል ነው መደምደሚያዬ።

በዛ ላይ ትናንትን ከዛሬም ከነገም በተሻለ የምናውቀው ቢሆንም አልፈየደም። ከባህሪው ላዛሬና ለነገ ልንጠቀምበት የምንችለው መፍትሄ አናገኝበትም። ካለም እጅግ በጣም ትንሽ ነው። ዛሬ መፍትሄያችንን የሚሻው ችግር ከትናንትን መሰረት ያደረገ ሲዋረድ የመጣም ቢሆንም እንኳ። ሂደት ነውና ችግሩ  ዛሬ የተለየ ባህሪና ቅርጽ ይይዛል። ስለዚህም ዛሬ ችግሩ ያለውን ይዘት ባህሪና ቅርጽዋና ትኩረት በማድረግመስራት ነው ትክክል የሚሆነው ነበር እሳቦቴ። ዘላቂነት እንዲኖረውና የማያዳግም እንዲሆን ደግሞ ነገን ግምት ውስጥ በማስገባት መፍትሄ መስራቱ   ነው ትክክለኛ አካሄድ አድርጌ የወሰድኩት። በነገራችን ላይ ዋና የሆነውን የፖለቲካ ልዩነት በተመለከተበዛም በዚህም በኩል ያሉት ችግሩ ትናንትን አለማወቃችን ነው በሚለው ይስማማሉ። አለመግባባቱም መፍትሄውንም ያከበደው ትናንት ስለማናውቅ፤ ስለምንክድ፤ማመን ስለማንፈልግ፤ ስለምንዋሽ ነውበሁሉም ጎን ያሉ የሚያቀርቡትመከራከርያ። ትናንትን በራሳቸው አረዳድ ማየቱ እነዳለ ማለት ነው። ስለዚህ በታሪክ ላይ አንድ አይነት የጋራ ግንዛቤ ላይ መድረስ ካልተቻለ ወይ ንቅንቅ። መቼም ደግሞ የምንደርስ አይመስለኝም።

አለመሳሳቴን እርግጠኛ ለመሆን በመጀመርያ ያደረኩት በመፀሀፉ ትናንት አለማወቅ ምክንያቶች ሆኖውየቀረቡ ጉዳዬች መመርመር ነበር።መፀሀፉ

በተናጠል በግለሰብ ደረጃ ማየት አለው። በግለሰብ ደረጃ ዛሬን አይደለም ነገም ላይ ችግር የለብንም። ሆዳችንን በመቀነት ቋጥረን ለነገ ቅሪት የምንሰበስብ ብዙ ነን። ችግሩ የጋራ ለሆኑ ጉዳዬች አገር፤መብት፤ መልካም አስተዳደር፤ መልካም አገልግሎት፤ ፍትህ፤ እኩልነት......የመሳሰሉ በጋራ ካልሆነ በቀላሉ የማንነቀንቃቸው ችግሮችና መፍትሄዋቻቸው ላይ ነው። ዘሬ መሀይም የሆነው።እንዴት?፤ ምን? መቼ?፤ከየት፤ ማን?፤ መደረግ ያለበት ጥንቃቄ? ለሚሉት መልስ የለንም። መፈለጉም ጠቃሚ ሆኖ የታየ አይመስልም።

ትናንትናን ማወቁ "እውቀት ነውና የማሰብ ችሎታችንን በማሳደግና በማስፋት፤በማነቃቂት፤ የችግሩን የኋላ ታሪክ አጥንቶ በተገቢው ለመረዳትና ዛሬ ላለብን ችግርና ተሻግረንም ለነገ ሁሉ መፍትሄ ለመስራት የሚኖረው ጠቀሜታ አሌ የማይባል ነው። በዚህ መንፈስ የቀረበውን ሙሉ በሙሉ እስማማበታለው። ዛሬና ነገን እንደሌሉ አድርገን ከሰጠነው ቦታ አኳያ ግን ጥቅሙ አይመጥንም። ትናንት መኖሩ በራሱ የዛሬ ችግር ላይ መፍትሄ ለመስራት ሳንካ የሚሆንባቸውን ሁኔታዎች ስንደምር ደግሞ ጥቅሙን የበለጠ ያሳንሰዋል።

በመፀሀፉ ትናንትናን ባለማስተወሳችን በሚል ምሳሌ ተደርገው ከቀረቡት ምክንያቶች አንዱን ላንሳና ለሌሎቹም መልስ የሰጠሁበትን መንገድ ላስቀምጥ።

እናት ኢትዬጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ፤
የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ፤

ባንዳ ነግሶ አርበኛ እንዲሳደድና እንዲያዝን የሆነው ትናንትን ካለማወቅ አይመስለኝም። በጊዜው ትናንት ዛሬ በነበረ ጊዜ ትክክለኛ ምርጫ ማድረግ አለመቻል ነው ችግሩ። ይህ ድርጊት ነገ ላይ የሚያስከትለውን ጦስ ባለማጤን የተሰራ ስህተት ነው። እንደውም ንጉሱ በግል ከገቡበት ችግር አኳያ መውጫ መፍትሄ ወደኋላ ሄደው ከትናንትና ያሰቡና ምን አልባትም የተመከሩ መሆኑ ለስህተቱ ምክንያት የሆነይመስላል።አርበኞቹም ያኔ ዛሬን ቆም ብለው አስበው ቢሆን ኖሮ ጥቃቱን በተሻለ መከላከል ወይ ማስቀረት ይችሉ ነበር። ትናንት መንግስትና ንጉሱ ላይ በነበረ እሳቦት መዘነጋታቸው ነው ያስጠቃቸው። ባጠቃላይ ትናንት ችግር ከነበረ መፍትሄ ካልተሰራለትም መፍትሄው ስህተት ከሆነም፤ በቂም ካልሆነ ትናንት ዛሬ በነበረበት ጊዜ የመስራት ችግር እንዳለን እንጂ የሚያሳየው ክትናንትና ወዲያን አለማወቅን አይደለም። ችግሮች ትናንት የጀመሩ የትናንት መሰረት ይኑራቸውዛሬ ነገን ሁሉ ግምት ውስጥ አስገብቶ በጊዜው መፍትሄ ሊሰራላቸው ይገባል። ለዛሬ ከተላለፈ የትናንት መሆኑ ቀርቶ የዛሬ የኛ ያሁኖቹ ችግር ነው። ዛሬም ነግን እያሰብን ካልሰራነውየልጆቻችን ችግር ይሆናል።ለልጆችን ካወረስነውደግሞ መፍትሄ ለመስራት ቁርጠኝነቱና መስራት የሚያስችለን እውቀቱ አለን የለንም ከሚለው ጋር ነው ቀጥተኛቁርኙቱ።

ትናንትናን እንጂ ዛሬን ላለማወቃችን አሳማኝ ምሳሌዎች።

እስከዛሬበስነ ፅሁፍ፤ በኪነ ጥበብ፤በኪነ ስእል ስራዎቻችንን በሙሉ አይቶ ምን ያህሉ ስለዛሬ፤ ምን ያህሉ ስለነገ፤ ምን ያህሎቹ ደግሞ ስለትናንት ያወራሉ የሚለውን ማየት ይቻላል። ማወቅ ያለብን ዛሬን እንደትናንት መተረክ ዛሬን ማወቅ በጭራሽ አይደልም። የዛሬን ችግር ባግባቡ ተረድቶ ሙሉ የሆነ መፍትሄ ምን አልባታም ካንድ በላይ ማስቀመጥና የተሻለውን መርጦ ተግባራዊ ማድረግ ካልተቻለምስራውን ዛሬመጀመር ነው ዛሬን ማወቅ።

ሌላው ጥናት ነው ሊባል ባይችልም ለስምንት አመታት ሻይና ቢራ እያስተናገድኩ የብዙ ደንበኞች የሚወያዩበትን፤ የሚከራከሩበትን፤ የሚጣሉበትን፤ የበዛ ጊዜ የሚሰጡትን ጉዳይ ለማየት ሞክሬያለው። ስለአገርና ህዝብ ከሆነ እጅግ የበዛውን ጊዜ የቀደመ ታሪክ ላይ መሆኑን ተገንዝቤያለው። በተመሳሳይ ዛሬ ላይ የየለትና በቅርብ መነጋገርያ በሆኑ አንኳር ጉዳዬች ላይ እንደምንወያይም እንዲሁ። ጠቅለል ሲደረግ ዛሬ ላይ በትንሹ መፍትሄ ድረስ በማይሄድ ነገን ላይ እስከጭራሹ እንደማንነጋገር ነው የተረዳሁት። ስለትናንት መወያየቱከድህንነት አኳያ ችግር ስለሌው ብቻ ግን አይደለም። ውይይቱ ላይ ተሳትፎ ለማድረግ የሚያስችለው እውቀት ሁሉም አለኝ ብሎ ስለሚያስብ በእርግጥም ስላለው ነው።የግድ የታሪክ ምሁር ያህል ሁላችንም ማወቅን አያሻም። አይፈልግምም።

ለነዚህ ረጅም አመታት እኔም ድርሻ ያደረኩበት ውይይት ሁሌ ትናንት ላይ ብቻ መሆኑ ስለመረረኝ የሆነ ጊዜ ላይ ስለትናንት ማውራቱ ብቻ ፋይዳ የለውም። ከዛሬ ጀምሮ መፍትሄ ድረስ በሚሄድ ስለዛሬና ስለነገ እንወያይ የሚል ሀሳብ አቅርቤ ተቀባይነት አግኝቶ ነበር። መነሻ የሚሆን ሀሳብ ለማቅረብ ቢሞከርምውይይቱ ብዙ አልሄድ አለ። ጊዜ አልበቃው ይል የነበረ ውይይትዝምታና መፋጠጥ ስለበዛበት ቀስ ብሎ ወደድሮው ልምድ ተመለሰ። ይህ የሆነው በትንሹ ካስር አመት በፊት ነው።

መንገድ በመንገድና ህንፃ በህንፃ ሆነች ተብላ ብዙ የተወራለትን አዲስ አበባ ላይለዚህች ትንሽ ስራየብዙ ዜጎችን ሂወት በእጅጉ ተመሳቅሏል። ብዙ እውቀት፤ገንዘብና ጉልበት ፈሶበታል። መነሻ ፍላጎቱማ ሀሳቡምዛሬ ነበር የተባለ ችግርን ለመቅረፍ

ነው። ባጠቃላይ ለነገ አይደለም ላዛሬ ችግር በማይሆንበት መንገድ ግን አልተሰራም። ለምን ማፍረስም መስራትም እንደጀመሩ በቅጡ እንኳን አያውቁም ነበር። አለማወቃቸውን እነሱም እያመኑ ነው። ትራፊክ ተጨናነቀ፤ የሚኪና አደጋ በዛ፤ ማቆሚያ የለም። ታክሲዎች ለመጫንና ለማውረድ ማቆም እንዳለባቸው እንኳ አልታሰበም። አረንጓዴ ቦታ አልተተውም።የሚባለው እውነት ከሆነና በሐይለስላሴ ጊዜ የተሰራ እቅድ ተጠቅመው ከሆነ ለምን ይህ እንደተፈጠረ ችግሩን ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል። ያው ተሰሩ የተባሉ ህንፃዎች መንገዶቹ ጫፍ ላይ ተደርድረዋል። ለማስተካከል እንደጋና ማፍረስ፤ እነደገና ማመሳቀልን ይፈልግብናል ማለት ነው።

አሜሪካኖች እኛ ዜግነት ለማግኘት አጥንተን የምንፈተነውን ፈተና ለሙከራ ተፈትነው ብዙዎቹ እንደማያልፉ ሲነገር ሰምቻለው። ለተላላቅ ሰዎቻቸው መዘክር፤ መታሰቢያ፤ ላይብረሪ ቢሰሩ የተሰራለትን ግለሰብ ጋር ተያያዥነት ያለቸውን ታሪክ መሰብሰብ ትንሿ ሀላፊነት ነው። እነዚህ ማእከላት ወና ትኩረት አድርገው የሚሰሩት ስለዛሬና ነገ ነው። ሌላ ብዙ አመት ደግሞ ታክሲ እየሰራው ብዙ አሜሪካኖችን አመላልሻለው።ብቻቸውን ሆነው በስልክ ወይ ካንድ በላይ ሆነው ሲሳፈሩ የሚወዩበትን አርስትና ይዘት ምን እንደሆነ ለማወቅ ሆን ብዬ አድምጫለው። አርእስቱ ቢለያይም ስለ ትናንትና ታሪክ ሲያወሩ የሰማሁበት ጊዜ እጅግ በጣም ውስን ነው። አብዛኞቹ ሰረተኞች ስለሆኑም ይሆናል በስራ ደረጃም ሆነ ከስራ ውጪ ባለ ጉዳይ ላይ መፍትሄ ድረስ በሚሄድ እንደውምብዙውን ጊዜ መፍትሄ ላይ እንደሆነ ግን በእርግጠኛነት መናገር እችላለው።

መጻፌ ካልቀረ ብዬ ነው እንጂ እንደሁሌው ከዚህ በላይ የፃፍኩትን ሁሉ እራሴን ችዬ ብጽፍበት እችል ነበር። ይሻል የነበረውም እሱ ነው። በዋናነት አዳፍኔ ላይ ለመፃፍ ምክንያት የሆነኝ ከዚህ በታች የማስቀምጠው አንድ ገፅ ላይ ያለች ሀሳብ ብቻ ነች። ቁንፅል ብትሆንም ትልቅ ጉዳይ አድርጌ ወስጃታለው።

‘እራሱን እንደነጻ ሰው፤ እንደግለሰብ ማየትና በዚያው መሰረት መወሰን የማይችል ፍጡር ከአየራልንድም ይምጣ ከስኮትላንድ ፤ ከኢትዮጵያ ይምጣ ከኬንያ ወይም ከሱማልያ ገና ዝቅተኛ የሰውነት ደረጃ ላይ ያለ ነው።ገና የራሱ ባለቤት አልሆነም ማለት ነው። ወደግለሰብነት ደረጃ ላይ ያልደረሰና የግለሰብነት የሀላፊነት ባለቤትነትን ያልተረዳ በሰውነት ደረጃው ዝቅተኛ ነው።አስከትለው ስልጣን መቼ ትለቃለህ ተብሎ ደንግጦ የሞተው መሪ ሲጠየቅ ድርጅቴ ነው የሚወስነው ሲል የመለሰው ላይ ያብራራሉ። በማስከተል “ይህንን ያልተማረ ወይም ያልተገነዘበ ግለስብ ከእንሰሳት ደረጃ አልወጣም። ነግረ ግን በዩኒቨርሲቲ የሚያስተምሩና የሚማሩ ሰዎች በጎሰኛነት ሕመም ተይዘው ማደግና መሻሻል የሚባሉት ነገሮች በየት በኩል ግብቶ ቦታ ያገኛል።” እያሉ ይቀጥላሉ።

በጥንቃቄ እንዳያስጠይቅና አሻሚ ለማድረግ አስበው እሳቸው በደብተራ አፃፃፍ በሚሉት ነው ያስቀመጡት። ለነገር ከሆነ የዝንብ ጠንጋራን ለሚያውቅ አይደለም ለማንም ቀና አሳቢ ሊተላለፍ የተፈለገው መልእክት ግን ግልፅ ነው። ለነገሩ መለስ ዜናዊም ቢሆን ያን በማለቱ ተሳስቷል ሊባል ይችላል እንጂ ከሳቸው እኩል ሰው ነው። ዝቅ ብለው እሳቸውም አባባሉን ብልጠትና ውሸቱን እንደሆነ ገልፀዋል። ታዲያ ብልጥ ስለሆነ ነው ከሰው ያነሰው። ወይስ ስለዋሸ?። እዚህ ላይ መለስ ማደነጋርያ ሆኖ ነው የገባው። ጎሰኛ አስተማሪና ተማሪዎቹም እንዲሁ።

ለማንኛውም ጎሰኛ የተባሉት መምህራንና ተማሪዎች ለዚህ ደረጃ የደረሱት ሆነ ሂወታቸውን እየኖሩና እየመሩ ያሉት እራሳቸውን ችለውእያሰቡና እየወሰኑ ነው።እኔ ነበርኩ የማስብና የምወስንላቸው መቼም አይሉም። በጎሳ ያስባሉ ሲባልም ጭንቅላታቸውን የሸረሪት ድር በመሰለ ነገር አገናኝተው አንድ ትልቅና ውስብስብ አይምሮ ፈጥረዋል ለማለትም አይደለም። ይህ ቢሆንም ምንኛ ድንቅ ነበር። ኢትዬጵያ አይደለችም አለም በታደለች። ስላሴዎችን መሰሉ። ለማለት የተፈለገው በኢትዬጵያ ስም ብቻ ካልሆነ ትናንሽ ማንነቶችን ለምን ይፈጥራሉ ነው። የሚጋሩት የተለዩ ችግሮች ቢኖርም እንኳ በኦሮሞነት ወይ በትግሬነትችግርም ቢኖርባቸው መናገር ወይ ለመሰማት መተባበር የለባቸውም ነው።

ዛሬ በወያኔ ኢሕአዲግ ስርአት ነፃነቴን አጥቻለው የምንል ግለሰብ ወይስ እኛ?። እኛ ነን። የጋራ ችግረችንን አውቀን፤ መፍትሄው ስንሰራ ተባብረንና መክረን አስማምተን ነው። ታዲያ ዝቅተኛ የሰውነት ደረጃ ላይ ነን ማለት ነው?።ትግሉ ውስጥ ድርሻ ያለው ሁሉ በግሉ ችግር አለ መፍቴሄም ይሻል፤ ለዚህም ትግሉ ላይ የድርሻዬን ማበርከት አለብኝ ብሎበደንብ አስቦበት ውሳኔ አድርጎ ይሳተፋል። ከሌሎች ጋር አስተዋፆውን ያስተባብራል። ታዲያ በሰውነትህያንስክ ነህ የሚያስብለው የትኛው ተግባሩ ነው።እኩል የተሻለስ የሚያደርገውስ?። ሰው መህበራዊ ፍጡር የሆነውስ በምንድን ነው?።

ጎሳም እንደቤተሰብ፤መንደር፤ብሔር፤ ብሔረሰብ፤ ያንድ አገር ህዝብ፤ ጥቁርህዘብ፤ጋናዊ፤ አረብ፤ክርሲቲያን…ማህበረሰብ ነው። ልዩነቱ በብዛቱ፤ በቆዳ ቀለሙ፤ በእምነቱና በሚኖርበት ቦታ ነው። ሁሉም ከግለሰብ በላይ የሆኑ የሰዎች ስብስብ ነው። እንደተለያየ ማህበረሰብነቱ ልዩ ባህሪ ያላቸው የጋራ ችግር ይኖረዋል። መጨፍጨፍ አድሎ መንቋሸሽ ….ሊኖርበት ይችላል። ወይ አለ ብሎ ካመነ በጋራ ሆኖ ቢታገል፤ ድምፁን ቢያሰማ፤ ቢቃወም፤ ቢዋጋ ጭምርበእንሰሳት ደረጃ ያለ የሚያደርገውምኑ ነው። ግለሰብ ሆኖ የዚህ የዛ ስብስብና ማህበረሰብ ሳይሆን የሚኖርስ ማነው። በቤተሰቡ ላይ የተቃጣን አደጋ በተለየ የማያይ አለ። በቤተሰብ ደረጃ የተለየ ፍላጎትስ የሌለው። ታዲያፀሀፊው ከኔ ከሰው ጋር እኩል አይደሉም ሲሉ ምን ለማለት ፈልገው ነው?።

ጎሳ ምንድን ነው፤ ጎሳስ ማነው የሚለው እንዳለ ጠቅለለል ባለ ሌኔ ይህ እነሱ ማለት! አራት አይን ያላቸው።እጃቸው ወገባቸው ላይ ያለ።ጅርባቸው ላይ አምስት ቀንድ ። አረንጓዴ ግራጫና ሀምራዊ ቀለም ያላቸው። ጭራቅ አይነት አስፈሪ አውሬዎች ናቸው የሚለው ገለፃ ተሻሽሎ መጣነው ።ከዚህ ደረጃ ተነስቶ ተሻሽሏል ማለት ለፈለገ ይችላል። ለኔ ግኔ ከኛ በላይ ጥሩ አሳቢና የተማረ ኢትዬጵያዊ የለም ከሚሉ። አሉልን ከምንላቸውአንዱ አይደለም

*ሁለቱም ፕሮፌሰሮች መስፍን ወልደማርያምና፤ ጌታቸው ሀይሌ ይህን ተራኪዎች መሆናቸው አሳፍሮኛል።በቃ አሁን ሴጣን የሚለውንአውሬ ነው።ነገርግን ሰው የሚመስልበሚል ነው ያሻሻሉት። ይህ ክሸፈት የተባለው ምን ያህል የከፋና ለምን እንደከሸፍን ምንጩንም ያየሁበት ነው።*

ለነገሩ ይህ ልዩ ፍጡር ቆንጆ ገፀ ባህሪ ለልጆች ይወጣዋል። የልጆች ስለሆነና የኦሮሞ ህዝብ የተሳለበት ስለሆነ ጥሩ ገፀ ባህሪና ብናላብሰው ጀግና ብናደርገውበልጆች በፍቅር የሚወደድ ካርቱን ይወጣዋል። ለነገ የተሻለ ዜጋ በመፈጠሩም አስተዋፆ አለው።ፍልሙ ሲጀምር አስገራሚ በሆነ ሁናቴ ባህሩ ይናጥና ከውሀ ውስጥ አውሬው ሲወጣ እናደርጋለን።

ግጥም አድርጌ እንደ ኦሮሞ አስባለው። እወስናለው። ነግር ግን እንደ ኦሮሞ ብቻ አላስብም። እንደ ዳዊት አስባለው። እንደ ዳባ ቤተሰብ፤ እንደኮንን ሰፈር ልጅ፤እንደጥቁር፤ እንደአፍሪካዊ አስባለው። እንደጁም አስብ ነበር። አሁን እንደ ፍልስጤምና እንደአፋር አስባለው እወስናለው▪▪▪▪። ፍትህ የተጓደለበት የተጨቆነ፤ የሚገደል▪▪ ባለበት ሁሉ ሳልፈልግ በመንፈስእዛ አለው።ስለዚህም ያ አውሬ እኔ ነኝ። ከርሶ በሰውነቴ አንሳለው ማለቴ ነው። እንደ ኢትዮጵያው የሚለውን አውቄ ነው የተውኩት። ሰው ለመሆን የግድ እንደ ኢትዮጵያዊ ማሰብ የለብኝም። ኢትዮጵያዊ ስለሆንኩ ግን ማሰብን ፈልጌየምተወው ፈልጌ የማደርገውምአይደለም።

ሐይለስላሴ የናታቸውን ማንነት አልደበቁም። የደበቁት ታሪከኞች ናቸው። በይበልጥም የንጉሱ ታሪክ ላይ የፃፉ። ያም ሆኖይህ ተደበቀ ታወቀ ይህን ያህል ፋይዳ የለውም። አሳሳቢው ሌላስ ስንት ነገር አውቀው ደብቀውናል የሚለው ነው። የየጁ ኦሮሞዎች ኢትዮጵያን አስተዳድረው ነበር የሚል አዲስ ታሪክ ብቅ እያለ ነው። እዚህ ታሪክ ላይ ትልቁ ጉዳይ ኦሮሞዎች መግዛት አለመግዛታቸው ሳይሆን ወይ ጎንደር ማእከል መሆኑ አለመሆኑ ወይ ስፋቱ አይደለም። ያስተዳደሩት ለምን ቀበሌ አትሆንም ዋናው ቁምነገር። እውነት ከሆነ ለመቶ ሀያ አመት በስምንት ገዳ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ተደርጓል። ይሄ ለኢትዮጵያዊያን እጃችንን ጭንቅላታችን ላይ አድርገን የሚያስጨበጭብ ብቻ ሳይሆን የሚያስጮህን ነው። ሀውልት ሊቆምለት የሚገባስ ይህ ነበር።

ከዚህ በታች ያሉትን ቁም ነገሮች በኦሮምነት አይደለም በጊዜው የወሰድኳቸው። በኢትዮጵያዊነትም አይደለም። በጣም ልጅ እያለው ለክረምት አያቶቼ ጋር ሄጂየተለዩ ስለሆኑወድጃቸዋለው። እያደኩ ስሄድ ደግሞ እጅግ ጥሩ፤ ትክክለኝ ነገሮች አድርጌ አስቤያቸዋለው። ስለዚህም ውስጤ ትልቅ ቦታ ይዘዋል። አሁን ግን በኦሮሞነት አስቤና ወስኜ እፅፋቸዋለው።

ፈታና ደስታ ያለበትን ጊዜ መርጠው በሰከነና ስርአት ባለው መልክ አንድን ችግረ ከስሩ መርምረው መፍተሄ መስራት እንደሚችሉ አይቻለው። ችግሮችን ለሌላ ጊዜ መቆየት ድረስበግዜያዊመፍትሄ ሰርተውለት ጊዜ ወስደው አክርመው ማየት እንደሚችሉና በመጨራሻ መፍትሄ እንደሚሰሩለትም እንዲሁ። ዛና የሚያደርገው ጊዜ ከሶስት ወር በኋላ የታህሳስ ቅዱስ ገብርኤል ንግስ ሊሆን ይችላል። ከያዙት ቁምነገር ጋር የሚያያዙና የሚመሳሰሉ ድንቅ ታሪኮች፤ አባባሎች፤ ቀልዶች ሁሌም በገፍ አላቸው። ጉዳዬ የግለሰብ ከሆነ ባለጉዳዬች እኩል መናገር ያለባቸውን ሁሉ እንዲናገሩ፤ እንዲከራከሩ ይደረጋል። እኔም፤ ሴቶች ልጆችም ውጡና ውጪ ተጫወቱ አልተባልንም።

ለተፈጥሮ መቆርቆርና መውደድ በገዘፈ መንገድ አይቻለው። ፀሎታቸው ሁሉ ስለተፈጥሮ ደህንነት ነው። ለደስታና ለዝና ሲሉ ለገደሉት እንሰሳ አምላክን ለመለማመን የፀሎትና የልመና ዝግጅቱ አንድ ዲል ያለ የሀብታም ሰርግ አድርጋችሁ ውሰዱት።ስለዚህ ዝም ብሎ መግደል ክልክል ነው። ውሻባጮጮሁ ወይ እራት ላይ መረሳቱን ካስታወሱ ለሊት ላይ ተነስተው ምጣድ ይጣዳሉ።ለውሻ ምግብ ማዘጋጀት የሰው እኩል የሁል ጊዜ ስራ ነው። እንክብካቤው ስላላቸው ዶሮዎች በየቀኑ እንቁላል ይጥላሉ። በቀን ሁለቴ የሚጥሉ ሁሉ ያየው ይመስለኛል። በስራ ላይ የዋለ እንሰሳ የተለየ እንክብካቤ አለው። ፈረስ በፍቅር ይወዳሉ። ይንከባከባሉ። ያሰውባሉ። እንሰሳትን ለስራ ስትጠቀምም ሆነ ስታግድ ለመመለስና ለመግራት ያህል እንጂ መደብደብ ሁሉንም ጨርቃቸውን ነው የሚያስጥላቸው። እንዲህ አድርግህ እንደመታህው በሽታ ወይ አምላክ ይምታህ ብሎ ሊያስረግምህ ይችላል። ሲያውሱ እንዳትመታብኝ፤ በተለየ ለብቻው እንድትመግበው ሲሉ ማሳሰብ ሁሌምየማይረሱት አደራ ነው። እረኛ ሆነህ ከብቶቹ ታከው የማይበላም ቢሆን እያደገ ያለ እፀዋትን ካጠፉ ያስገስፃል። ሲያደርጉ አይቼ ግራር ከስሩ ስቆርጥ አላፍ ገበሬ ዝልጦኛል። ከቆረጡ በምትኩ ወይ መልሶ ማደግ አለበት ይላሉ▪▪▪▪።

ለህፃናት ለሴቶችና ለአቅመ ደካሞች ከለመድኩትና ከማውቅ በተለየ እንክብካቤ ያደርጋሉ። ህፃናት በፍቅር ይወዳሉ። ዱላ እጅግ ያልተለመደ ነው። ህፃናቱ ከፍ ሲሉ ሴቶችም ነፃነታቸው በተሻለ ከኢኮኖሚ ነፃነት ጋር ነው።ይህ ምን ማለት እንደሆነ መቼም ይገባናል። ከቁም ነገር ቆጥረውን በየቀኑ ቁጭ አድርገው ህፃናትንያወሩናል። ያጫውቱናል። በመጠየቅና በተረት፤ ታሪክ በመንገር ያስተምራሉ። የሚለብሷቸው ልብሶች አብዛኛው ከተሜ ከሚለብሳቸው በላይ ወጋቸው ውድ ነው። በነሱ የፍትህ ስስርአት ሽምግልና ልጆችም ሴቶችም እኩል ይዳኛሉ።ቤተሰብ ሲያወራ እንደሰማሁት ትንሽ መሬትና ጥቂት ከብቶች የነበራት አርበኛዋ አያቴ ያልወለደቻቸውን ሀያ ስድስት ህፃናትን አሳድጋለች።

ባህላዊም ቢሆን የሚጠቀሙባቸው ቁሳቁስ ድንቅ የጅ ስራ ውጤቶች ናቸው። ዱላ መያዝ እንወዳለን። ዱላው ዝም ብሎ ከዛፍ ላይ ተቆርጦ የሚያዝ እንዳይመስለን። በፍለጋ ለማዘገጃት የሚወስደውን ጊዜ የሚደረግለትን እንክብካአቤ ብታዩት ሁልሽም በኖረኝ የምትይው ነው። ከልብስ ከለር ጋር አስማምቶ ለመያዝ በአይነት ነው ያላቸው። የተለየ አይነት የበዓላት አከባበር አላቸው። በተለይመስቀል። አዲስ አመታቸው ነው መሰለኝ።በአሉን ሰዎች ብቻ አይደሉም እንሰሳቱም ናቸው የሚያከብሩት። አንዱ ችቦ አዲስ አበባ ደመራ ብለን በየቤታችን የምንሰራውን ያክላል። መሸከም ስለማልችል እሱ በትከሻ ይዞ

እኔ የጎረምሳውን ልብስ ይዤ ነው በመከተል ችቦው የኔ የሚሆነው። ጅራፉ አራት መአዘን ነው።  የሚተኩሱት ወደፊት ወደላይናወደታች ነው። ከፈለጉ ወደላይ ወደታች ወደጎን አከታትለው ሶስቴ ይተኩሳሉ።ይህቺ በሁለት ክረምት በልጅነቴካየኋት በትንሹ ነው። የኖረበት ብዙ ሊል ይችላል።

የኦሮሞ ህዝቡ ድሮም ዛሬም ቅሬታ ይዞ ነው የሚኖረው። በኔ ግንዛቤ አናኗሩ የዚህ አይነት የስልጡን ህዝብ ነው። ቅሬታው  ኑሩ የተባልነው ወደኋላ የሚመልስንና ኋላ ቀር ነው የሚል ነው። የተሻል ካላችሁ አምጡ። አለበለዛ ተውን የራሳችን ይሻለናል ነው። እውነታቸውን ነው ብግድ ካልኖራችሁ ስንለው የነበረው አሁን እኛም የከሸፈ ነው እያልን ነው። ያኔ እኔ የማውቃቸው በሙሉ እራሳቸውን ኢትዮጵያዊም አድርገው ነው የሚያዩት። አርበኛ፤ወዶ ዘማቾች፤ ሚሊሻ፤ ወታደሮች ብብዛት አሉበት። ለዝች አገር ነብስና አካላቸው የገበሩም ብዙ ናቸው።

ለፈለገ መፃፍን መተቸትን አልከለክልም። ዳዊት ይህን ሰለፃፍክ ወይ ይህን ወይ ያንኛውን ስላልክ ወይ ስላደረክ ከኔ ወይ ከኛ ታንሳለህ ሊለኝ ለሚፈልግ ሁሉ መልሴ አንድ ነው። ይህንን ለናትህ ንገራት። ለምን እራሱ አምላክ አይመጣም። በተመሳሳይ አንተ ዘረኛ ነህ ለሚለኝ ሲጀመር እኔ ካንተ በሰውነት እበልጣለው ብሎ ማሰብ ነው ዘረኝነት ነው መልሴ።በዛ ላይ ሙብራት ይዘህ በገበያ መሀል ስትፈልግ ብትኖር የኦሮሞ ዘረኛ የለም። ምን አልባት ብሶተኛ ያስኬዳል።" ጠባብ ነህ"። እኔ ጠብቤ ሳይሆን አንተ ጠብህ ነው ሊሆን የሚችለው። የምናወራው በሁሉም መልክ ስለሰፊ ጉዳይ ነው። ጤፍን በሲኒ መስፈር ልምድ አድርገህ እንዳይሆን።ቆም ብለህ እራስህን ጠይቅ ነው መልሴ። የበታችነት ይሰማሀል። አልክ? ይጥላኝ ብልህ መፍጠርህም አይደንቀኝ። ያው ከዚህ የተለየ አይኖርም ብዬ ነው።

ዘርኝነት ድንቁርና ነው። ደንቁራችሁ አታዳናቁሩን።